# በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢሕጤኢ

መጋቢት 2008 ቅጽ 1 ቁጥር 6 — በኢሕጤኢ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ወርሃዊ መደበኛ ስብሰባ ተካሂደ



የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፈታት በየካቲት እና መጋቢት ወር 2008 ዓ.ም በወጣው እቅድ መሰረት የውስጥና የውጪ ደንበኞች ያቀረቡት አስተያየት ችግሮቹ መፈታታቸውን ለማረጋገጥ በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ሰብሳቢነት የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች መጋቢት 30/2008 ዓ.ም ውይይት አካሂደዋል፡፡

የውይይቱ ዋና አላማም በኢንስቲትዩቱ የተለዩትን የውጪና የውስጥ ደንበኞች አስተያየት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በአፋጣኝ በመፍታት የተገልጋዮችን እርካታ ለማረጋገጥ ታስቦ የተዘጋጀ ውይይት ነው፡፡

በህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት በኩል በወቅቱ የተተነተነ ሪፖርት ለማኔጅመንትና ለሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች በጽሁፍ ከማቅረቡም በላይ በመልካም አስተዳደር ችግሮች ዙሪያ በታህሳስ፣ በጥር እና በየካቲት ወር መሰራት ይጠበቅባቸው የነበሩትን ዝርዝር ተግባራት

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ሴቶችና ወጣቶች ከተለያዩ በሽታዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ የሚያስችል ስልጠና ተሰጠ



የኢንስቲትዩቱ ሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት የእብድ ውሻ በሽታ ምልክቶችና መከላከያው፣ የጡትና ማህጸን ካንሰር በሽታ ምልክቶች እና መከላከያ ዘዴያቸው በሚሉ ርእሶች ዙሪያ በጉለሌ ክ/ከተማ ስር ለሚገኙ 49 ለሚሆኑ ሴቶችና ወጣቶች ከመጋቢት 15-18/2008 ዓ/ም በኢንስቲትዩቱ አዳራሽ ስልጠና ሰጠ፡፡

ወ/ሮ ሙኒት መኩሪያ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ኤክስፐርት የስልጠናውን ዋና አላማ እንደገለጹት በእብድ ውሻ በሽታ እና በጡትና በማህጸን ጫፍ ካንሰር ዙሪያ ያሉትን ቅድመ መከላከያና ጥንቃቄ በሚገባ ግንዛቤ በማስጨበጥ ሰልጣኞቹ በክ/ከተማና በወረዳዎች ትምህርት እንዲሰጡ ታስቦ የተዘጋጀ ስልጠና ነው ብለዋል።

ሃላፊዋ ስልጠናውን አስመልክቶ እንደ አብራሩት ስልጠናው እንደተጀመረ ጤናማ ምግብ ምን ማለት እንደ ሆነ የተለያዩ የምግብ አይነቶች ያላቸውን የምግብ ይዘት፣ ሴቶች እራሳቸውን ከማህጸን ጫፍ ካንሰር እንዴት ቅድመ መከላከል እንደ ሚያደርጉ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን በቀጣዩ ቀን ደግሞ የእብድ ውሻ በሽታ ሲከሰት ሊታዩ የሚችሉ ምልክቶች እና ሊደረጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል ብለዋል።

ሃላፊዋ በመጨረሻም እንደገለጹት ሰልጣኞች በስርአተ ጾታ ዙርያ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር የስረአተ ጾታ ምንነትና የህይወት ክሕሎት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በቀረበው ስልጠና ላይ ሰልጣኞች በቡድን በመወያየት አንድ አይነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ሲሉ አብራርተዋል።

# በኢንስቲትዩቱ የካይዘን ትግበራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በተመረጡ አራት ዘርፎች በግቢ ውበትና ጽዳት ከልቡ፣ በንብረት አስተዳደር ከልቡ፣በሪከርድና ማህደር ከልቡ እና በቢሮ አስተዳደር ከልቡ የካይዘን ፍልስፍና አሰራርን በሚገባ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ተገለጸ።

አቶ ሁሴን ፋሪስ የኢንስቲትዩቱ አቅርቦትና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኢንስቲትዩቱ የካይዘን ፍልስፍና አሰራር ትኩረት ስለመሰጠቱ ሲያብራሩ በተቋሙ ውስጥ በሪከርድና ማህደር በኩል የማህደር መደርደሪያዎች ተሰርተዋል፣በርካታ የፋይል ማቀፊያ ተገዝተዋል፣የጉዳይ ፋይሎችና የሰራተኛ ፋይሎች እንዲሁም የቆዩ ፋይሎችና ወቅታዊ ፋይሎች ተለይተው የማያስፈልጉትን በማስወገድ ላይ እንገኛለን ብለዋል።

ዳይሬክተሩ አያይዘው እንደገለጹት የግቢ ውበትና ጽዳትን በተመለከተ ከሶስተኛው የኢንስቲትዩቱ ሳይንቲፊክ ኮንግረንስ ጋር በማያያዝ በቅንጅት እየሰሩ እንደሚገኙ እና ለዚህም ያገለገሉ ብረቶች የመሸጥ ስራ መሰራቱን፣በቀጣይ ደግሞ በኢንስቲትዩቱ ያሉ እንጨቶችን የማስወገድ ስራ ለመስራት በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ አብራርተዋል።

ሃላፊው በተጨማሪም እንዳብራሩት ደረጃውን የጠበቀ የታካሚ መጸዳጃ መገንባት እና የቆዩትን ደግሞ የማደስ ስራ እንዲሁም የመኪና ማቆሚያ በማሳተካከል ላይ የሚገኙ ሲሆን የአትክልት እና የቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን በመለየት እቃዎች የመግዛት ስራ መሰራቱን አብራርተዋል።

ሃላፊው በኢንስቲትዩቱ ግቢ ውስጥ የሚገኘውን የሰራተኞች ክበብ ዘመናዊና ውበቱን የጠበቀ ከማድረግ ጋር ተያይዞ እየተሰራ ያለውን ሲያብራሩ የምግቡን ጥራት ለማስጠበቅ በግቢው ውስጥ መጋዘን የምግብ ማብሰያ ቤት ለማስራት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን እና ይህም የግቢውን ውበት ከመጠበቅ አንጻር ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ገልፀዋል።

በመጨረሻም ሃላፊው እንዳስቀመጡት የማይስፈልጉ ኬሚካሎችን የማስወገድ ሂደቱን በተመለከተ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኬሚስትሪ ትምህርት ክፍል ፕሮፖዛሉን አዘጋጅተው የላኩልን ሲሆን በኢንስቲትዩታችን በኩል ተወያይተን ስንጨርስ ተፈራርመን ወደ ስራ በቅርብ ቀን ይገባል ብልዋል።



ቀድሞ የነበረው የማህደር አያያዝ /በስተግራ/ እና ከካይዘን ትግበራ በኋላ

# በኢንስቲትዩቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እየተፈቱ መሆናቸው ተገለጸ

በኢንስቲትዩቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ችግሮቹ ተለይተው ወደ ስራ ከተገባ ጊዜ ጀምሮ በተቋሙ በውጪና በውስጥ ደንበኞች ይቀርቡ የነበሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በተሸለ ሁኔታ እየተፈቱ መሆናቸው ተገለጸ፡፡

አቶ አቤል የሻነህ የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ሃላፊ እንደገለጹት በኢንስቲትዩቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በተሸለ ሁኔታ እየተፈቱ ነው ለዚህም በእንግዳ መቀበያ ተጽፎ የነበረው አላስፈላጊ ጥቅስ መነሳቱ፣ለውጪና ለውስጥ ደንበኞች ሃሳብ መሽጫ መዝገብ እና ሳጥን ከመግቢያ በር ጀምሮ በግ

> ...እንዲሁም ሰራተኞች ትርፍ ጊዜቸውን የሚሳልፉበትን የእስፖርት ሜዳ ተጠርጎ ስራው በሂደት ላይ መሆኑ....

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በኢንስቲትዩቱ አዲስ ለተቀጠሩ ሰራተኞች በስነ-ምግባር ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የስነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት በመልካም አስተዳደር ምንነት፣በ



ሙስና ጽንሰ ሃሳብ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት በሚሉ ርእሶች ዙሪያ 50 ለሚሆኑ በኢንስቲትዩቱ አዲስ ለተቀጠሩ ሰራተኞች በሁለት ዙር በተቋሙ አዳራሽ ስልጣና ሰጠ።

አቶ ፉፋ ዳባ የስነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት ሃላፊ የስልጠናውን ዋና አላማ ሲገልጹ እንዳብራሩት የተቋሙን ሰራተኞች ስለ መልካም አስተዳደር እና ስለ ሙስና ጽንሰ ሃሳብ ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ በማስጨበጥ በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የሚፈጠሩትንና ለሙስና በር የሚከፍቱትን መንገዶች ለመዝጋት ታስቦ የተዘጋጀ ስልጠና ነው ብለዋል።

ሃላፊው አያይዘው እንደገለጹት በሃገር ደረጃ በመልከም አስተዳደርና በሙስና ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማጥፋት መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል በመሆኑም እንደ ተቋማችንም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እና የሙስና አስተሳሰቦችን ለማጥፋት እየሰራን እንገኛለን ሲሉ አብራርተዋል።

በጨረሻም ሃላፊው እንዳስቀመጡት ሰልጣኞች ከዚህ ስልጣና በኋላ የግልጸኝነትን አሰራር በመረዳት ደንበኞችን በመልካም ተቀብሎ ማስተናገድን ባህላቸው ከማድረግም በላይ በመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት የሚፈጠሩትን ችግሮች በመጋፈጥ አጥፊዎች አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ተብሎ ይታሰባል ብለዋል።

---

ከገጽ 1 የዞረ

## . .ሰራተኞች ወርሃዊ መደበኛ

በመለየት ዳይሬክቶሬቶቹ በጽሁፍ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ለዋና ዳይሬክተር እና ለም/ዋና ዳይሬክተሮች የመግልጽ ስራ እንደተሰራ በውይይቱ ወቅት ተገልጿል::

በዚህ መሰረትም በውጪ እና ውስጥ ደንበኞች በኩል ለተነሱት የተለያዩ ችግሮች የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች ችግሮቹ የተከሰቱበት ምክንያት እና ችግሮቹን ለመፍታት እየተደረገ ያለውን ጥረት ከመግለጻቸውም በላይ በተቋሙ በኩል ችግሮቹ ሊፈቱ የሚችሉበትንም መንገዶች ላይ አስተያየት ሰጥተዋል::

የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀ ዝርዝር እቅድ በአቶ አረጋ ዘሩ በእቅድና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የቀረበ ሲሆን ተግባራዊ አፈጻጸሙም በሚፈለገው ደረጃ እንዳልሆነ የሚያሳይ መሆኑን አስረድተዋል::

በሪፖርቱ ዙሪያ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አመሃ ከበደና ም/ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ይበልጣል አሰፋ አስተያየት ተሰጥቶበታል::

በውጪ ደንበኞች የተነሱ ቅሬታዎችን የክልል ላብራቶሪ አቅም ግንባታ፣የአቅርቦትና ፋይናንስ፣ የጠቅላላ አገልግሎትና የሰው ሃብት ዳይሬክቶሬቶች በጋራ በመገናኘት በአጭር ጊዜ የሚፈቱትን በመፍታት በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የሚፈቱትን ደግሞ በመለየት የጊ

> ....በእለቱ የተካሄደው ስብሰባ ከዚህ ቀደም ከተካሄዱት ውይይቶች በሰራተኛው ተሳትፎም ሆነ በተነሱት ፍሬ ሃሳቦች በጣም መሻሻል የታየበት መሆኑንና .....

ዜ ሰሌዳ አዘጋጅተው በየሳምንቱ ለማኔጅመንት ሪፖርት እንዲያደርጉ ከስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን የቀረቡት የተላያዩ ችግሮችን የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች እስከ ሚዚያ አጋማሽ በመፍታት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ተወስኗል::

በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ እንደተነሳው በእለቱ የተካሄደው ስብሰባ ከዚህ ቀደም ከተካሄዱት ውይይቶች በሰራተኛው ተሳትፎም ሆነ በተነሱት ፍሬ ሃሳቦች በጣም መሻሻል የታየበት መሆኑንና በቀጣይ የሚካሄደው ጠቅላላ ስብሰባ በኢንስቲትዩቱ የሚታዩትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ከመፍታት አንጻር ከውጤት ሊያደርሱ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የሁሉም ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያስፈልግ መሳሰቢያ ተሰጥቶበታል::

እያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት የሚሰራበትን መመሪያና ደንብ አትሞ በማዘጋጀት ለደንበኞች በሚታይ ምቹ ቦታ ማስቀመጥ እንዳለበትና የተሰጠውን ሃላፊነትና የስራ ድርሻ በመወጣት እንዲሁም ወደ ተግባር በመቀየር በየሳምንቱ ሪፖርት ለማኔጅመንቱ እንዲያቀርብ ተወስኖ የእለቱ የውይይት ስብሰባ ተጠናቋል::

. . .በኢንስቲትዩቱ የመልካም አስተዳደር

ከገጽ 2 የዞረ

ቢው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች
መዘጋጀታቸው፣በውጪና በው
ስጥ ደንበኞች አስተያየት መሰ
ረት ከሃላፊዎች ጋር በተደረገ
ው ውይይት በርካታ ችግሮች መ
ፈታታቸው እንደ አንድ ማሳያ ነ
ው ብለዋል፡፡
ሃላፊው አያይዘው እንደገለጹት በ
እንግዳ መቀበያ የውጤት መዘግየ
ት ይታይ ነበር ነገር ግን ከሚመ
ለከታቸው ክፍሎች ጋር በመነጋ

> ...ከመግቢያ በር ጀምሮ በ
> ግቢው ውስጥ በተለያዩ ቦ
> ታዎች መዘጋጀቱ፣ በው
> ጪና በውስጥ ደንበኞች አ
> ስተያየት መሰረት ከሃላፊ
> ዎች ጋር በተደረገው ውይ
> ይት በርካታ ችግሮች መፈ
> ታታቸው እንደ አንድ
> ማሳያ....

ገርና ችግሩ ምን እንደሆነ በመለ
የት ለችግሩም አቅጣጫና መፍት
ሄ በመስጠት ውጤቱ ሳይቆራ
ረጥ እና በተሸለ ፍጥነት እየተ
ሰጠ ሲሆን ከፌደራል ሆስፒታ
ሎች ናሙናዎች የላብራቶሪ ድ
ጋፍ አገልግሎት ከ750 ባላይ በ
መቀበል በቀን እስከ ምሽቱ 4 ሰአ
ት ድረስ በመስራት ከፍተኛ ድጋ
ፍ እየተደረገ ይገኛል ይህም የተ
ቋሙን ሰራተኞች ጥንካሬ የሚያ
ሳይ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡
ሃላፊው በጨረሻም እንደገለጹት
በኔትዎርክ መቆራረጥ ምክንያት
የነበረውን የመረጃ በወቅቱ ያለመ
ድረስ ችግር ለመቅረፍ ከአይሲቲ
ክፍል ጋር በመሆን ከፍተኛ ጥረ
ት እየተደረገ ነው እንዲሁም ሰ
ራተኞች ትርፍ ጊዜቸውን የሚሳ
ልፉበትን የእስፖርት ሜዳ ተጠር
ጎ ስራው በሂደት ላይ መሆኑ የ
መልካም እስተዳደር ችግሮች በተ
ሻለ መንገድ በመፈታት ላይ መ
ሆናቸውን ያመለክታሉ ሲሉ ተና
ግረዋል፡፡

# ወቅታዊ መረጃ

## የህዳሴ ግድብ ጥሬ ሃቅ

የመሰረት ድንጋይ መጋቢት 24
ቀን 2003 ዓ.ም. በታላቁ መሪ ክ
ቡር አቶ መለስ ዜናዊ ተጣለ፣
የግድቡ ስፍራ፡- ቤንሻንጉል ጉ
ሙዝ ክልላዊ መንግሥት/ ጉባ፤
ግንባታው የሚካሄደው፡- በአባይ
ወንዝ ላይ
የሚያመነጨው ኃይል፡- 6000
ሜጋ ዋት
የፋይናንስ ምንጭ፡- የኢትዮጵያ
መንግሥት እና የኢትዮጵያ ብ
ሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች።
ዋና ዋና ተግባሮች፡- ሲቪል ኤሌ
ክትሮ ሜካኒካል፣ ሃይድሮ ሜካኒ
ካል፣ የአካባቢ ጥበቃና መልሶ ማ
ቋቋም፣
የግንባታ ጊዜ ሰባት ዓመታት ው
ስጥ ኃይል ማመንጨት ይጀመ
ራል።
ዋናው ግድብ፡-145 ሜትር ከፍታ
1,780 ሜትር ርዝመት
ቴክኖሎጅ፡- ዋናው የኮንክሪት ግ
ድብ አጠቃላይ ከሚሞላው 10.1
ሚሊዮን ኪዩቢክ ሜትር መጠን
ያለው የRCC ሙሌት ውስጥ እ
ስከ መጋቢት 10/2008 ዓ.ም 5.5
ሚሊዩን ኪዩቢክ ሜትር ተሞል
ቷል።
ሳድል ዳም፡-50 ሜትር ከፍታ፣
5.2 ኪሎ ሜትር ርዝመት፣ 15
ሚሊዮን ኪዩቢክ ሜትር መጠን
የድንጋይ ሙሌት (Rock Fill) የ
ሚፈልግ ሲሆን እስከ መጋቢት
10/2008 ዓ.ም 5.2 ኪዩቢክ ሜት
ር መጠን የድንጋይ ሙሌት ተከ
ናውኗል።
የኃይል ማመንጫ ጣቢያ፡- በግድ
ቡ ግርጌ በስተቀኝ 10 ዩኒት፣ በ
ግድቡ በስተግራ ስድስት ዩኒት፣
እያንዳንዳቸው የሚያመነጩት
ኃይል 375 ሜጋ ዋት በዓመት
15,692 ጊጋ ዋት ሰዓት ያህል ኃ
ይል ያመነጫል፣ የኃይል ማከፋ
ፈያ ጣቢያው ባለ 500ኪሎ ቮል
ት መጠን ይኖረዋል።
የኃይል ማስተላለፊያ መስመር፡-
240 ኪሎ ሜትር ርዝምት ያለው
ባለ 400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማ
ስተላለፊያ መስመር ግንባታው እ
የተጠናቀቀ ይገኛል።፤
620 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው
ባለ 500 ኪሎ ቮልት የኃይል ማ
ስተላለፊያ መስመር በግንባታ ላ
ይ ይገኛል።
የኤሌክትሮ ሜካኒካል እና ሃይድ
ሮ ሜካኒካል ስራዎች፡- ዲዛይን፣
ምርት፣ አቅርቦት፣ ተከላ እና ፍ
ተሻ በኢፌዴሪ ብረታ ብረት እና
ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን እየተከና
ወነ ይገኛል።
የአባይ ወንዝን እንደገና የመቀል
በስ ስራ ተሰርቷል፣ ከፍተኛው የ
ውኃ ልክ 640 ሜትር ከባህር ጠ
ለል በላይ ሲደርስ ነው።
የሚሸፍነው ቦታ 1,874 ስኩየር
ኪሎ ሜትር የሚደርስ ነው፣
ውኃው ከግድቡ 246 ኪሎ ሜት
ር ርዝመት ያህል ወደኋላ ይተኛ
ል፣ ውኃው ከባህር ጠለል በላይ
640 ሜትር መጠን ሲያልፍ በቀ
ላሉ የሚያስተነፍሱ 3 በሮች አ
ሉት፣
የአካባቢ ጥበቃ እና መልሶ ማቋ
ቋም ስራዎች፡- 110 ኪሎ ሜትር
ርዝመት ያለው ከአሶሳ ማንኩሽ
የሚያገኛኝ ተለዋጪ መንገድ፣ ከ
ዋናው ግድብ በታች አምስት ኪ
ሎ ሜትር ርቀት ላይ 240 ሜት
ር ርዝመት ያለው ድልድይ ግን
ባታ፣ ዉሃው በሚተኛበት አካባቢ
ያሉ ነዋሪዎችን መልሶ የማስፈር
ስራ፣ 123,000 ሄክታር የምንጣሮ
ስራ ተከናውኗል።
በግንባታ አካባቢ የህክምና አገል
ግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ፣
የባንክ አገልግሎት፣ የፖስታ አገ
ልግሎት፣ እና የጉሙሩክ እና ት
ራንዚት አገልግሎቶች ተሟልተ
ዋል።
ሌሎች መረጃዎች፡-
የታላቁ የህዳሴ ግድብ በዓለም እ
ስከ አሁን ከተገነቡ ግድቦች ጋር
ሲነጻጸር 8ኛ ደረጃ ሲሆን ከአፍ
ሪካ የመጀመሪያው ግዙፉ ግድብ
ይሆናል።
በአሁኑ ወቅት 317 የውጪ አገር
ባለሙያዎች፣ 10,355 ኢትዮጵያ
ውያን፣ 2,300 በላይ የሆነ የተለ
ያዩ ማሽነሪዎች በግንባታው ላይ
ይገኛሉ።